የኢትዮጵያ
ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ)
ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COUNCIL (EHRCO)

# የኢሰመጉ የደ/ብ/ብ/ሕ ክልል ህዝበ ውሳኔ መታዘብ ቀዳሚ መግለጫ

የካቲት 02/2015 ዓ.ም

## መግቢያ፡

**የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ)** ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ባገኘው ሕጋዊ የህዝበ ውሳኔ ገፅ ለገፅ የመራጮች ስልጠና እና ምርጫ ታዛቢነት ፈቃድ መሠረት 22 ታዛቢዎችን ለማሠማራት ከፍተኛ ዝግጅት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በተጨማሪም የአሰልጣኞች ስልጠና በተሰጣቸው የገፅ ለገፅ የመራጮች አሰልጣኞችን በማሰማራት 4 የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ካምፕን ጨምሮ 1680 መራጮች የገፅ ለገፅ ስልጠና እንዲወስዱ አድርጓል።

እንደሚታወቀው ጥር 29 ቀን 2015 ዓ.ም በደብብህክ መንግስት በሚገኙ 6 ዞኖች ( ወላይታ፣ ጌዲኦ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ኮንሶ እና ደቡብ ኦሞ) እና 5 ልዩ ወረዳዎች ( ደራሼ፣አሌ፣ቡርጂ፣አማሮ እና ባስኬቶ) የደቡብ ኢትዮጵያ የሚባል አዲስ ክልል ለመመስረት ወይም በደብብህክ ውስጥ እንደነበሩ ለመቀጠል የህዝበ ውሳኔ ድምፅ የአካባቢው ነዋሪዎች ሲሰጡ ውለዋል፡፡

ኢሰመጉም ከህዝበ ውሳኔው ቀን በፊት እና የምርጫው ዕለት ያሉትን የምርጫውን ሒደቶች በወላይታ፣ ዲላ፣ጋሞ፣ ኮንሶ፣ ደራሼ እና አሌ ባሰማራቸው 22 ታዛቢዎቹ ምልከታና ክትትል ያደረገ ሲሆን በዚህም 19 ምርጫ ጣቢያዎችን በቋሚነት እና 70 ምርጫ ጣቢያዎችን በመዘዋወር በመታዘብ በድምሩ 89 የምርጫ ጣቢያዎችን መመልከት ችሏል።

ይህ ዘገባ የተዘጋጀው በዋናነት ኢሰመጉ ካሠማራቸው ታዛቢዎች የተሰባሰቡ መረጃዎችን በመጠቀም ሲሆን፤ የምርጫው ዕለት በኢሰመጉ አርባምንጭ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የኩነቶች መቆጣጠሪያ ክፍል የተቀበሏቸው ጥቆማዎችና አቤቱታዎች እንዲሁም ሲከናወን ከቆየው የሚዲያ ክትትል በተገኙ መረጃዎች በግብዓትነት በመጠቀም ነው፡፡

በመግለጫው የተካተቱት በዋናነት በድምጽ መስጫው ዕለት በሒደቱ የታዩ ዋና ዋና ነጥቦች ብቻ ሲሆኑ፤ ጥቅል የምርጫ መታዘብ ሥራውን ግኝቶች ሁሉም ታዛቢዎቻችን የሞሏቸው ቅጻ ቅጾች ወደ ዋናው የምርጫ ጉዳዮች ክፍል ተጠቃለው ከገቡና ዝርዝር ትንታኔ ከተሠራባቸው በኋላ ይፋ የሚደረጉ ይሆናል፡፡ ይህ ቀዳሚ መግለጫ የተዘጋጀው ከምርጫው ቀን ቀደም ብሎ፣ በዕለቱ እና በምርጫ ጣቢያዎች ውጤት በተለጠፈበት ዕለት በተሰባሰቡ መረጃዎች ብቻ በመሆኑ፤ በቀጣይ ተጨማሪ መረጃዎች ሲገኙ ሊለወጡ የሚችሉ የይዘት እና ምልከታ ለውጦች ሊኖሩ እንደሚችሉ አስቀድመን እንገልጻለን።

## ከድምጽ መስጫው ዕለት ቀደም ብሎ የነበሩ ኩነቶች፡

- ታዛቢዎቻችን ለመታዘብ በተንቀሳቀሱባቸው ቦታዎች በሙሉ በሙሉ አካባቢው ተለጽፎ የሚታው የዕርግብ (የደቡብ ኢትዮጵያ) ምልክት ብቻ እንጂ አንድም ቦታ ማለት አስኪቻል ድረስ የጎጆ ምልክት ( የደብብህክ) አለመኖሩ፤
- የውድድር መንፈስ ለህዝበ ውሳኔም ይሁን ማንኛውም ምርጫ ወሳኝ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ጎጆን ወክለው የሚያስረዱ አካላት አለመኖራቸው፤
- የፌዴራልም፣ የክልል፣ የዞን እና የልዩ ወረዳን ባለስልጣናት ጨምሮ እስከ ታችኛው የመንግስት እርከን ድረስ ያሉ አመራሮች ስለ አዲሱ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል አስፈላጊነት በማስረዳት መራጩ ህዝብ እርግብን መምረጥ እንዳለበት እየቀሰቀሰ የነበረ ቢሆንም፤ በጎጆ ወገን ግን ይህንን ማድረግ የሚያስወግዝ እና እንደክህደት ስለሚቆጠር ምንም አይነት ቅስቀሳ አለመታየቱን፣
- የምርጫ ጣቢያዎች በበርካታ ስፍራዎች በቀበሌ እና በመንግስት ድርጅቶች ቅጥር ግቢ ውስጥ ተመስርተው ተመልክተናል፣
- ከምርጫው አንድ ቀን ቀደም ብሎ ጨምሮ በምርጫ ጣቢያዎች በቅርበት አንዳንዴም ምርጫ ጣቢያው በር ላይ ሳይቀር የዕርግብ ምልክት ያለበት ፖስተር ተለጥፎ አስተውለናል፡፡

## በድምጽ መስጫው ዕለት የነበሩ መልካም አጋጣሚዎች፡

- ቀደም ሲል በመራጮች ምዝገባ ወቅት የተቀዛቀዘ ይመስል የነበረው የዜጎች የምርጫ ተሳትፎ በምርጫው ቀን ድምጻቸውን ለመስጠት በተለይ በማለዳው እና በጠዋቱ ክፍለ ጊዜያት ለሰዓታት ተሰልፈው ለመምረጥ የነበራቸው ከፍተኛ ፍላጎት፤
- በታዘብንባቸው ምርጫው በተከናወነባቸው አካባቢዎች በሁሉም ማለት እስኪቻል ድረስ የጎላ የጸጥታ መደፍረስ ችግር ሳያጋጥም የድምፅ አሰጣጥ ሒደቱ በሰላማዊ ሁኔታ መጠናቀቁ፤
- በየደቂቃው የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታትና እንዳይፈጠሩም ለመከላከል የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ዋና አመራሮች ጭምር ያሉበት የግንኙነት መስመር
- መዘርጋቱና ችግሮችን ወዲያውኑ ለማስተካከል ያደረገው ጥረት፤
- አብዛኛው ምርጫ ጣቢያ ውጤቱን ምሽቱን ቆጥሮ መለጠፍ መቻሉ ናቸው፣
- የምርጫ ቦርድ በአጠቃላይ የምርጫ ሂደት የምርጫ ስራችንን በመልካም ሁኔታ ለማስኬድ በቅርብ አብሮን እየሰራ መሆኑ ናቸው።

## በድምፅ መስጫው ዕለት የተስተዋሉ ዋና ዋና ችግሮች፡-

- በታዘብንባቸው አንዳንድ አካባቢዎች አስፈላጊ ዝግጅቶችን ቀድሞ ማድረግ ሲገባ በዕለቱ ለመስራት የተሞከሩ ዳሶች ፀሐይን የሚከላከሉ ባለመሆኑ ታዛቢዎችም ሆኑ አስፈጻሚዎቹ ምቹ በሆነ ሁኔታ ምርጫውን መከታተል አለመቻላቸው፣ እንዲሁም በተመቻቸ ሁኔታ ያልተቀመጡ ድንኳኖች ወድቀው የምርጫ ሂደቱን ቢያውኩም በርብርብ ሰዎች ላይ አደጋ እንዳይደርስ መከላከል ተችሏል፣
- ታዛቢዎቻችን ከተሠማሩባቸው ምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ 12:00 ሲል የጀመረው በውስን የምርጫ ጣቢያዎች ላይ ሲሆን፤ በተወሰኑ ስፍራዎች የተወሰኑ ደቂቃዎችን ዘግይተው የተከፈቱ መሆናቸው።
- ታዛቢዎቻችን በተሠማሩባቸው በአብዛኛዎቹ ምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ የድምፅ አሰጣጥ ሒደቱ ከመጀመሩ አስቀድሞ ሊያዙ የሚገባውን ቃለ-ጉባኤ በአብዛኛው ቦታዎች አለመያዝ
- መራጩ ለምርጫ ሲመጣ የመታወቂያ ካርዱን መያዝ እንዳለበት የሚታወቅ ቢሆንም በአብዛኛው የምርጫ ጣቢያዎች የተመዘበበበትን የምርጫ ካርድ በመያዝ ብቻ ምርጫውን ሲያካሂድ ውሏል፣
- ምንም እንኳን ጥቂት ቦታዎች ቢሆንም የሚስጢር ክፍልን በመጋረጃ የመከለል ስራ አስተውለናል፣
- የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ ያዘጋጀውን ለመራጮች ስለሂደቱ ግንዛቤኖሯቸው እንዲመርጡ የሚያደርግ ማስተማሪያ ዶክመንት በአብዛኛው ስፍራዎች አለመጠቀም፣
- የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ በመምረጫ ሳጥኖች ላይ እንዲለጠፉ የሰጣቸውን ኮዶች አንዳንድ ምርጫ ጣቢያዎች አለመለጠፋቸው
- በአንዳንድ ምርጫ ጣቢያዎች ያሉ የምርጫ አስፈጻሚዎች ስለምርጫው አካሄድና አሰራር የግንዛቤ ማነስ፣
- በአንዳንድ ምርጫ ጣቢያዎች እድሜያቸው ለመራጭነት ያልደረሱ መራጮችን ተመልክተናል፣
- የድምፅ አሰጣጥ ሒደቱን እንዲያስተባብሩና እንዲመሩ በሕግ ከተፈቀደላቸው የምርጫ አስፈጻሚዎች ውጪ ከምርጫ ቦርድ ባጅ ያልተሰጣቸው የቀበሌ አመራር፣ የቀበሌ ጸጥታ አስከባሪዎች፣ መራጮችን ተራ በማስያዝ፣ ስለ ድምፅ አሰጣጡ ትምህርት በመስጠት፣ ሚስጢራዊ ቦታዎች አካባቢ በማስተባበር እና በመሳሰሉት ሥራዎች ላይ በርካታ ምርጫ ጣቢያዎች ላይ ሲሥሩ ተስተውሏል፣
- ካለው ውስን የምርጫ አስፈጻሚዎች አቅም አንጻር አንድ መራጭ በአማካኝ በአንድ ጣቢያ ውስጥ የሚኖረው ቆይታ ከ 2 ደቂቃ በላይ የተራዘመ መሆኑ፤ መራጮች ለረዥም ሰዓት ተራቸውን በመጠበቅ እንዲያሳልፉ እና የምርጫው ሰዓት እስከ ምሽት 3:00 ድረስ እንዲገፋ በመደረጉ፤ የምርጫ አስፈጻሚዎች ላይ ከፍተኛ ጫና አሳድሯል።
- በውጤት ላይ ከዚህ ቀደም ታዛቢ የማይፈርም ሲሆን በህዝበውሳኔን በተመለከተ በተዘጋጀው ዶክመንት ላይ ታዛቢ ውጤት ላይ መፈረም እንዳለበት የተቀመጠ ሃሳብ እንዳለ በግልጽ ከምርጫ አስፈጻሚዎች መረጃ ባላገኙ ታዛቢዎች እና አስፈጻሚዎች መከካል አለመግባባት መከሰቱ፣
- የመራጭት ካርድ የጠፋባቸው መራጮቸ ያለመታወቂያ ካርድ እንዲመርጡ መፍቅድ፣
- ስልጠና ያልወሰዱ ምርጫ አስፈጻሚዎች መኖር፣
- የምርጫ አስፈጻሚዎቸ ከተወለዱበት አካባቢ በመመልመላቸው ነፃ መሆን እንዳይችሉ ተፅዕኖ ማሳደሩ፣
- በአንዳንድ ምርጫ ጣቢያዎች የምርጫው ሰአት እንዲራዘም የቀበሌ አመረሮች ግፊት መታየቱ፣
- በአብዛኛው ጣቢያ ምንም ታዛቢ አለመኖር፣
- ምንም እንኳን በህዝበ ውሳኔ መመሪያው ዕውቅና ተቀባይነት የሚያገኙ ድምጾች ራይት፣ ኤክስ፣ አሻራ ወይም ግልጽ የሆነ ምልክት የሚል ቢሆንም፤ ውስን ምርጫ ጣቢያዎች ፊርማን እንደግልጽ ምልክት በማሰብ አንዳንድ ስፍራዎች የምርጫ አስተባባሪዎችም መመሪያ ታክሎበት ማንነትን ሊገልጽ የሚችለውን ፊርማን ተቀባይነት የሚያገኝ ድምጽ አድርጎ መቁጠር፡፡

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ